Seattle
Office of Labor Standards

# የሲያትል Office of Labor Standards (OLS, የስራ መደብ ቢሮ)- ለስደተኛ እና ለጥገኛ ያለን መሰጠት

## <u>OLS የጥገኛንና የስደተኛን መብት ይጠብቃል</u>

የሲያትል Office of Labor Standards (OLS) በሲያትል ከተማ ውስጥ የስራ መደቦችን ለማሻሻል ሁሉንም የሲያትል ሰራተኞችና ነጋዴዎችን ለማገልገል ዝግጁ ነው። የደሞዝ ስርቆት በስደተኞችና በጥገኞች መካከል በሰፊው ያለና በብዛት የማይዘገብ ነው። OLS የስደተኝነት ሁኔታዎችን ሳያይ ለሁሉም ሰዎች በነጻ አገልግሎት ይሰጣል። እነዚህ አገልግሎቶች የሚያጠቃልሉት የተፈጠሩ የስራ መደብ መተላለፎችን መመርመር፣ ሰራተኞችንና ነጋዴዎችን እየወጡ ማግኘት፣ መረጃዎችን እና ጥቆማዎችን መስጠት።

ለሲያትል ስደተኛ እና ጥገኛ ማህበረሰቦች ጠቃሚ መረጃዎች፡

- OLS በፍጹም ስለ ስደተኝነት ሁኔታ እና የስደተኝነት ሁኔታ ሰነዶችን አይጠይቅም።
- OLS የነጻ የቋንቋ ማስተርጎምና ትርጉም አገልግሎት ይሰጣል።
- OLS በሲያትል ከተማ ውስጥ የሚገኝ ዲፓርትመንት ሲሆን ከፌደራል መንግስት ጋር የማይገናኝና መረጃዎችን የማይለዋወጥ አካል ነው።

ሲያትል እንግዳ ተቀባይ ከተማ የሆነበት ምክንያት ሁሉንም በማጠቃለልና በእኩልነት ስለምናምን ነው። የከተማው ሰራተኞች ስለዜግነት ሁኔታ የማይጠይቁና ሁሉንም ነዋሪዎች የስደተኝነት ሁኔታ ሳይጠይቁ በእኩል የሚያገለግሉ ናቸው። ስደተኞችና ጥገኞች እዚህ ተቀባይነት አላቸው።

## <u>OLS የሰራተኞችን መብት ያስጠብቃል</u>

የትም ይኑሩ የትም፣ በሲያትል ውስጥ **የሚሰሩ** ከሆነ፣ **የስራ መደብ መብትዎ የሚያጠቃልሉት፡**

- ቢያንስ በሲያትል ውስጥ ያለውን ዝቅተኛ የደሞዝ ክፍያ እንዲያገኙ፤
- ለሰሩበት እያንዳንዱ ሰዓት ክፍያ እንዲያገኙ፤
- እርስዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል ታሞ ከሆነ እና ስራ መሄድ ካልቻሉ የህመም ፈቃድ ወጥተው ያልሰሩበትን ጊዜ ክፍያ የማግኘት መብት፤
- አሰሪዎ መበቴን ጥሷል ብለው ካመኑ ለ OLS የማመልት መብት፤ እና
- ለ OLS አመልክተው በምርመራ ውስጥ የሚሳተፉ ከሆነ ስምዎንና መረጃዎን ሚስጥራዊ የማድረግ መብት።

## OLS ሰራተኞች ላይ ከሚደረግ የበቀል ድርጊት ይጠብቃል

የሲያትል ህግ የስራ መደብ ጥሰት ዘገባ ያቀረበ ሰራተኛ ላይ የሚደርስን የበቀል ድርጊት ይከላከላል፡፡ **አሰሪዎች በሰራተኞቻቸው ላይ የበቀል ድርጊት በሚከተሉት መንገድ የሚያደርጉ ከሆነ ህገወጥ ነው፡**

- ለስደተኛ መንግስት አካላት አንድ ሰራተኛ ወይም የቤተሰብ አባላቱ ህጋዊ ሰነድ እንደሌላቸው ማሳወቅ ወይም ማስፈራራት፤
- ከመንግስት ኤጀንሲ ጋር የውሸት ሪፖርት ማቅረብ፤ እና
- ከስራ መደብ መቀነስ ወይም ማባረር፡፡

ምንም እንኳን ለእኛ የስራ መደብ ቅሬታ በማቅረብዎ ምክንያት የበቀል ድርጊት እንደማይደርስብዎ ባናረጋግጥም፣ በሰራተኞች ላይ የበቀል ድርጊት በሚያደርጉ አሰሪዎች ላይ ግን ተገቢውን ቅጣት እንዲቀበሉ እናደርጋለን፡፡ **የበቀል ድርጊት እንደደረሰብ የሚያስቡ ከሆነ ወይም የስራ መደብ ጥሰት እንደደረሰብዎ የሚያስቡ ከሆነ ወይም ስለ መብትዎ ጥያቄ ካለዎት OLS ን በ ሚቀጥለው አድራሻ ያግኙ፡** 206-256-5297, workers.laborstandard@seattle.gov፣ **ወይም** http://www.seattle.gov/laborstandards/investigations/file-a-complaint::

**ንግድ ኖሮት ስለ ስራ መደብ ጥያቄ ካለዎት OLS ን በሚቀጥለው አድራሻ ያግኙ፡** 206-256-5297 **ወይም** business.laborstandards@seattle.gov.

OLS ከማህበረሰቡ እና ከንግድ ድርጅቶች ጋር የስራ መደቦችን በተመለከተ እና የውጪ ግንኙነቶችን በተመለከተ የውል ስምምነት ያደርጋል፡፡ በቀጥታ OLS ን ማግኘት ምቾት የማይሰጥዎት ከሆነ፣ ስለ መብትና ግዴታዎት ያለዎትን ጥያቄዎች አንዱን አጋራችንን በማግኘት መጠየቅ ይችላሉ፡፡

## ተጨማሪ መረጃዎች

*በስራ ቦታ ላይ ለ ስደተኝነት ተፈፃሚነት ድርጊት እየተዘጋጁ ላሉ ሰራኞች እና ነጋዴዎች፡*

- What to Do If Immigration Comes to your Workplace (ኢሚግሬሽን ወደ ስራ ቦታዎ ቢመጣ ምን ማድረግ እንዳለብዎ) (በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ ታይ፣ ኮሪያን፣እና ቻይንኛ ማግኘት የሚቻል)፣ የቀረበው በ National Immigration Law Center እና National Employment Law Project (ብሄራዊ የቅጥር ህግ ፕሮጀክት)፣ እና

- የኢሚግሬሽን ተፈጻሚነትን በመተመለከተ እገዛ, በዋሺንግተን አቶርኒ ጀነራል የቀረበ፡፡

*ለ DACA ተቀባዮች*

- የሲያትል ከተማ Office of Immigrant and Refugee Affairs (የስደተኞችና የጥገኞች ጉዳዮች ቢሮ) DACA ድረ ገጽ፣ መሰረታዊና እና ነጻ መረጃ የያዘ DACA (Deferred Action for Childhood Arrivals፣ ለመጡ ህጻናት የዘገየ ምላሽ) በሲያትል አካባቢ እና ዙሪያ በከተማው ማህበረሰብ እና በአጋሮች የሚዘጋጁ የእገዛ ኩነቶች፡፡

- Northwest Immigrant Rights Project (ኖርዝ ዌስት የስደተኛ መብቶች ፕሮጀክት) DACA መረጃ ገጽ፤ እና
- ብሄራዊ ድርጅት Here to Stay ጠቃሚ ድረ ገጽ፣ የአእምሮ ጤና አያያዝ ምክሮችን ጨምሮ፡፡

ስለ ሲያትል የስራ መደብ እና ስለመብትዎ ጥያቄ ካለዎት OLS ን በሚከተለው ማግኘት ይችላሉ workers.laborstandards@seattle.gov፣ ወይም 206-256-5297 ይደውሉ፡፡